# ቅንድበ መላጣ

ህዝብ እየተራበ ፤ የሚቀመሰው ጠፍቶ
መኖር እያቃተው ፤ ሰው ፤ ባገሩ ለፍቶ
ተምሮ ቦዘኔ ፤ አገሬው ፤ ሥራ አጥቶ
አይን ያወጣ ፤ ውሸት ፤ በቅጥፈት ተሞልቶ
ዘጠና በመቶው ፤ በጠኔ ተደፍቶ
ኢኮኖሚው ያድጋል ፤ ሁሌ ፤ አስር በመቶ ።

ዜጋ ፤ መስራት አይችል ፤ አስረው ፤ እግርና እጁን
ሰው ማብላት ፤ አቅቶት ፤ የወለደው ልጁን
ምጽዋት ሲጠብቅ ፤ እያየ ፤ ደጅ ደጁን
የልመና መንግስት ፤ አምላኪ ፈረንጁን
ያረብ ተላላኪ ፤ ሊያስደስት ወዳጁን
የማፍረስ ተልዕኮ ፤ ተይዞ ግዳጁን
እየቸረቸረ ፤ ያጦፋል ሀራጁን
የሸጠው ይሆናል ፤ ከመቶ ፤ አስር እጁን ።

የዳሩ አገር ፤ አልቆ ፤ መሀል እየሸጠ
ያገር ፤ የደሀ ሀብት ፤ ዘርፎ የናጠጠ
ችጋር ፤ ጠኔ ነግሶ ፤ ህዝብ እያናወጠ
ሥራ ፈቱ ፤ በዝቶ ፤ ጎልቶ እያፈጠጠ
ኢኮኖሚ አደገ ፤ ባስር ሸመጠጠ
ብሎ የሚዘላብድ ፤ የተዘረጠጠ
በውሸት ተቃኝቶ ፤ በውሸት ያበጠ
ኑሮው ፤ ቁልቁል እንጂ ፤ መቼ ተለወጠ?
ቅንድበ መላጣ ፤ ጠግቦ የማገጠ
ወሮበላ መንግስት ፤ ባገር አላገጠ ።

ታዛቢው … March, 03, 2010